# ሰቆቃወ ፡ ኤርምያስ ።

(ክለሳ.1.20020507)

## ሰቆቃወ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ።

ምዕራፍ ፡ 1 ።

1 ፤ አሌፍ ። ሕዝብ ፡ ሞልቶባት ፡ የነበረች ፡ ከተማ ፡ ብቻዋን ፡ እንዴት ፡ ተቀመጠች! በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ታላቅ ፡
የነበረች ፡ እንደ ፡ መበለት ፡ ኾናለች ፤ በአውራጃዎች ፡ መካከል ፡ ልዕልት ፡ የነበረች ፡ ተገባር ፡ ኾናለች ።

2 ፤ ቤት ። በሌሊት ፡ እጅግ ፡ ታላቅሳለች ፥ እንባዋም ፡ በጉንጯ ፡ ላይ ፡ አለ ፤ ከውሽማዎቿ ፡ ኹሉ ፡ የሚያጽናናት ፡
የለም ፤ ወዳጆቿ ፡ ኹሉ ፡ ወነጀሏት ፡ ጠላቶችም ፡ ኾኗት ።

3 ፤ ጋሜል ። ይሁዳ ፡ ስለመጨነቅና ፡ ስለባርነት ፡ ብዛት ፡ ተማረከች ፤ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ተቀመጠች ፡ ዕረፍትም ፡
አላገኘችም ፤ የሚያስጨንቋት ፡ ኹሉ ፡ ተጨንቃ ፡ አገኟት ።

4 ፤ ዳሌጥ ። ወደ ፡ ዓመት ፡ በዓልም ፡ የሚመጣ ፡ የለምና ፡ የጽዮን ፡ መንገዶች ፡ አለቀሱ ፤ በሮቿ ፡ ኹሉ ፡ ፈርሰዋል ፡
ካህናቷም ፡ እየጮኹ ፡ ያለቅሳሉ ፤ ደናግሎቿም ፡ ተጨነቁ ፡ ርሷም ፡ በምሬት ፡ አለች ።

5 ፤ ሄ ። ስለኀጢአቷ ፡ ብዛት ፡ እግዚአብሔር ፡ አስጨንቋታልና ፥ አስጨናቂዎቿ ፡ ራስ ፡ ኾኑ ፥ ጠላቶቿም ፡
ተከናወነላቸው ፤ ሕፃናቷ ፡ ባስጨናቂዎች ፡ ፊት ፡ ተማርከዋል ።

6 ፤ ዋው ። ከጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ውበቷ ፡ ኹሉ ፡ ወጥቷል ፤ አለቃዎቿ ፡ ማሰማሪያ ፡ እንደማያገኙ ፡ ዋላዎች ፡
ኾኑ ፤ ከሚያባርሯቸው ፡ ፊት ፡ ተዳክመው ፡ ኼዱ ።

7 ፤ ዛይ ። ኢየሩሳሌም ፡ በጭንቀቷና ፡ በመከራዋ ፡ ወራት ፡ ከጥንት ፡ዠምሮ ፡ የነበረላትን ፡ የከበረን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡
ዐሰበች ፤ ሕዝቧ ፡ በአስጨናቂዎች ፡ እጅ ፡ በወደቀ ፡ ጊዜ ፡ የሚረዳትም ፡ በሌላት ፡ ጊዜ ፥ አስጨናቂዎች ፡ አይዋት ፡
በመፍረሷም ፡ ሣቁ ።

8 ፤ ሔት ። ኢየሩሳሌም ፡ እጅግ ፡ ኀጢአት ፡ ሠርታለች ፤ ስለዚህ ፥ ረክሳለች ፤ ያከብሯት ፡ የነበሩ ፡ ኹሉ ፡ ኀፍረተ ፡
ሥጋዋን ፡ አይተዋታልና ፥ አቃለሏት ፤ ርሷም ፡ እየጮኸች ፡ ታለቅሳለች ፥ ወደ ፡ ኋላም ፡ ዘወር ፡ አለች ።

9 ፤ ጤት ። አደፏ ፡ በልብሷ ፡ ዘርፍ ፡ ነበረ ፤ ፍጻሜዋን ፡ አላሰበችም ፤ ስለዚህ ፥ በድንቅ ፡ ተዋርዳለች ፥ የሚያጽናናትም ፡
የለም ፤ አቤቱ ፥ ጠላት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሏልና ፥ መከራዬን ፡ ተመልከት ።

10 ፤ ዮድ ። አስጨናቂው ፡ በከበረ ፡ ነገሯ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ዘረጋ ፤ ወደ ፡ ጉባኤኽ ፡ እንዳይገቡ ፡ ያዘዝኻቸው ፡
አሕዛብ ፡ ወደ ፡ መቅደሷ ፡ ሲገቡ ፡ አይታለችና ።

11 ፤ ካፍ ። ሕዝቧ ፡ ኹሉ ፡ እየጮኹ ፡ ያለቅሳሉ ፡ እንጀራም ፡ ይፈልጋሉ ፤ ሰውነታቸውን ፡ ለማበርታት ፡ የከበረ ፡
ሀብታቸውን ፡ ስለ ፡ መብል ፡ ሰጥተዋል ፤ አቤቱ ፥ ተጐሳቍያለኹና ፡ እይ ፥ ተመልከትም ።

12 ፤ ላሜድ ። እናንተ ፡ መንገድ ፡ ዐላፊዎች ፡ ኹሉ ፥ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ምንም ፡ የለምን ፦ እግዚአብሔር ፡ በጽኑ ፡
ቍጣው ፡ ቀን ፡ እኔን ፡ እንዳስጨነቀበት ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ እንደተደረገው ፡ እንደእኔ ፡ መከራ ፡ የሚመስል ፡ መከራ ፡
እንዳለ ፡ ተመልከቱ ፥ እዩ ።

13 ፤ ሜም ። ከላይ ፡ እሳትን ፡ ወደ ፡ ዐጥንቴ ፡ ሰደደ ፡ በረታችበትም ፤ ለእግሬ ፡ ወጥመድ ፡ ዘረጋ ፡ ወደ ፡ ኋላም ፡
መለሰኝ ፥ አጠፋኝም ፡ ቀኑንም ፡ ኹሉ ፡ አደከመኝ ።

14 ፤ ኖን ። የኀጢአቶቼ ፡ ቀንበር ፡ በእጁ ፡ ተይዛለች ፤ ታስረው ፡ በዐንገቴ ፡ ላይ ፡ ወጥተዋል ፤ ጉልበቴን ፡
አደከመ ። ጌታ ፡ በፊታቸው ፡ እቆም ፡ ዘንድ ፡ በማልችላቸው ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠኝ ።

15 ፤ ሳምኬት ። ጌታ ፡ ኀያላኔን ፡ ኹሉ ፡ ከውስጤ ፡ አስወገዳቸው ፤ ጕልማሳዎቼን ፡ ያደቅ ፡ ዘንድ ፡ ጉባኤን ፡
ጠራብኝ ፤ ጌታ ፡ ድንግሊቱን ፡ የይሁዳን ፡ ልጅ ፡ በመጥመቂያ ፡ እንደሚረገጥ ፡ አድርጎ ፡ ረገጣት ።



www.ethiopianorthodox.org

16 ፤ ዔ ። የሚያጽናናኝ ፡ ነፍሴንም ፡ የሚያበረታት ፡ ከእኔ ፡ ርቋልና ፥ ስለዚህ ፡ አለቅሳለኹ ፤ ዐይኔ ፥ ዐይኔ ፡ ውሃ ፡ ያፈሳል ። ጠላት ፡ በርትቷልና ፥ ልጆቼ ፡ ጠፍተዋል ።

17 ፤ ፌ ። ጽዮን ፡ እጇን ፡ ዘረጋች ፤ የሚያጽናናት ፡ የለም ፤ እግዚአብሔር ፡ በያዕቆብ ፡ ዙሪያ ፡ ያሉትን ፡ እንዲያስጨንቁት ፡ አዘዘ ፤ ኢየሩሳሌም ፡ በመካከላቸው ፡ እንደ ፡ ርኩስ ፡ ነገር ፡ ኾናለች ።

18 ፤ ጻዴ ። በአፉ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ዐመፅ ፡ አድርጌያለኹና ፥ እግዚአብሔር ፡ ጻድቅ ፡ ነው ። እናንተ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፥ እባካችኹ ፡ ስሙ ፥ መከራዬንም ፡ ተመልከቱ ፤ ደናግሎቼና ፡ ጕበዛዝቴ ፡ ተማርከው ፡ ኼዱ ።

19 ፤ ቆፍ ። ውሽማዎቼን ፡ ጠራኹ ፥ እነርሱም ፡ አታለሉኝ ፤ ካህናቴና ፡ ሽማግሌዎቼ ፡ ሰውነታቸውን ፡ ያበረቱ ፡ ዘንድ ፡ መብል ፡ ሲፈልጉ ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ሞቱ ።

20 ፤ ሬስ ። አቤቱ ፥ ተጨንቄያለኹና ፥ አንዠቴም ፡ ታውኮብኛልና ፥ ተመልከት ፤ ዐመፃን ፡ ፈጽሞ ፡ አድርጌያለኹና ፡ ልቤ ፡ በውስጤ ፡ ተገላበጠብኝ ፤ በሜዳ ፡ ሰይፍ ፡ ልጆቼን ፡ አጠፋ ፡ በቤትም ፡ ሞት ፡ አለ ።

21 ፤ ሳን ። እኔ ፡ እየጮኽኹ ፡ እንደማለቅስ ፡ ሰምተዋል ፤ የሚያጽናናኝ ፡ የለም ፤ ጠላቶቼ ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ መከራዬ ፡ ሰምተዋል ፤ አንተ ፡ አድርገኸዋልና ፥ ደስ ፡ አላቸው ፤ ስለ ፡ ርሱ ፡ የተናገርኸውን ፡ ቀን ፡ ታመጣለኽ ፡ እነርሱም ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ ይኾናሉ ።

22 ፤ ታው ። ልቅሶዬ ፡ እጅግ ፡ ነውና ፥ ልቤም ፡ ደክሟልና ፥ ክፋታቸው ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ፊትኽ ፡ ይድረስ ፥ ስለ ፡ ኀጢአቴ ፡ ኹሉ ፡ እንዳደረግኽብኝ ፡ አድርግባቸው ።

## ሰቆቃወ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ምዕራፍ ፡ 2 ።

1 ፤ አሌፍ ። ጌታ ፡ በቍጣው ፡ የጽዮንን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አደመናት! የእስራኤልን ፡ ውበት ፡ ከሰማይ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ጣለ ፥ በቍጣውም ፡ ቀን ፡ የእግሩን ፡ መረገጫ ፡ አላሰበም ።

2 ፤ ቤት ። ጌታ ፡ የያዕቆብን ፡ ማደሪያዎች ፡ ኹሉ ፡ ዋጠ ፥ አልራራምም ፤ በመዓቱ ፡ የይሁዳን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ዐምባዎች ፡ አፈረሰ ፥ ወደ ፡ ምድርም ፡ አወረዳቸው ፤ መንግሥቱንና ፡ አለቃዎቿን ፡ አረከሰ ።

3 ፤ ጋሜል ። በጽኑ ፡ ቍጣው ፡ የእስራኤልን ፡ ቀንድ ፡ ኹሉ ፡ ቀጠቀጠ ፤ ቀኙ ፡ እጁን ፡ ከጠላት ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መለሰ ፥ በዙሪያውም ፡ እንደሚባላ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ነበልባል ፡ ያዕቆብን ፡ አቃጠለ ።

4 ፤ ዳሌጥ ። ቀስቱን ፡ እንደ ፡ ጠላት ፡ ገተረ ፥ እንደ ፡ አስጨናቂ ፡ ቀኙ ፡ እጁን ፡ አጸና ፥ ለዐይንም ፡ የሚያምረውን ፡ ኹሉ ፡ ገደለ ፤ በጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ድንኳን ፡ መዓቱን ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ አፈሰሰ ።

5 ፤ ሄ ። ጌታ ፡ እንደ ፡ ጠላት ፡ ኾነ ፥ እስራኤልን ፡ ዋጠ ፤ አዳራሾቿን ፡ ኹሉ ፡ ዋጠ ፥ ዐምባዎቿን ፡ አጠፋ ፤ በይሁዳም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሐዘንና ፡ ልቅሶ ፡ አበዛ ።

6 ፤ ዋው ። ማደሪያውን ፡ እንደ ፡ አትክልት ፡ ነቀለ ፤ የበዓሉን ፡ ስፍራ ፡ አጠፋ ፤ እግዚአብሔር ፡ በጽዮን ፡ ዓመት ፡ በዓሉንና ፡ ሰንበቱን ፡ አስረሳ ፥ በቍጣውም ፡ መዓት ፡ ንጉሡንና ፡ ካህኑን ፡ አቃለለ ።

7 ፤ ዛይ ። ጌታ ፡ መሠዊያውን ፡ ጣለ ፥ መቅደሱን ፡ ጠላ ፥ የአዳራሾቿንም ፡ ቅጥር ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ ፤ ድምፃቸውን ፡ እንደ ፡ ዓመት ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጉ ።

8 ፤ ሔት ። እግዚአብሔር ፡ የጽዮንን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ቅጥር ፡ ያፈርስ ፡ ዘንድ ፡ ዐሰበ ፤ የመለኪያውን ፡ ገመድ ፡ ዘረጋ ፥ እጁን ፡ ከማጥፋት ፡ አልመለሰም ፤ ምሽጉና ፡ ቅጥሩ ፡ እንዲያለቅሱ ፡ አደረገ ፤ በአንድነት ፡ ደከሙ ።

9 ፤ ጤት ። በሮቿ ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ሰጠሙ ፥ መወርወሪያዎቿን ፡ አጠፋ ፡ ሰበረም ፤ ንጉሧና ፡ አለቃዎቿ ፡ ሕግ ፡ በሌለባቸው ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ አሉ ፤ ነቢያቷም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ራእይ ፡ አላገኙም ።

10 ፤ ዮድ ። የጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ተቀምጠዋል ፤ ትቢያን ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ነሰነሱ ፥ ማቅም ፡ ታጠቁ ፤ የኢየሩሳሌም ፡ ደናግል ፡ ራሳቸውን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ አዘነበሉ ።

11 ፤ ካፍ ። ሕፃኑና ፡ ጡት ፡ የሚጠባው ፡ በከተማዪቱ ፡ ጐዳና ፡ ላይ ፡ ሲዝሉ ፥ ዐይኔ ፡ በእንባ ፡ ደከመች ፥ አንዠቴም ፡



www.ethiopianorthodox.org

ታወከ ፤ ስለወገኔ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ቅጥቃጤ ፡ ጉበቴ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተዘረገፈ ።

12 ፤ ላሜድ ። በከተማ ፡ ጐዳና ፡ እንደ ፡ ተወጋ ፡ ሰው ፡ በዛሉ ፡ ጊዜ ፥ ነፍሳቸውም ፡ በእናቶቻቸው ፡ ብብት ፡ በወጣች ፡ ጊዜ ፥ እናቶቻቸውን ፦ እኽልና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ ይሏቸዋል ።

13 ፤ ሜም ። የኢየሩሳሌም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ምን ፡ እመሰክርልሻለኹ ፧ በምንስ ፡ እመስልሻለኹ ፧ ድንግሊቱ ፡ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ አጽናናሽ ፡ ዘንድ ፡ በምን ፡ አስተካክልሻለኹ ፧ ስብራትሽ ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ ታላቅ ፡ ነውና ፤ የሚፈውስሽ ፡ ማን ፡ ነው ፧

14 ፤ ኖን ። ነቢያትሽ ፡ ከንቱና ፡ ሐሰተኛ ፡ ራእይ ፡ አይተውልሻል ፤ ምርኮሽንም ፡ ይመልሱ ፡ ዘንድ ፡ በደልሽን ፡ አልገለጡም ፤ ከንቱና ፡ የማይረባ ፡ ነገርንም ፡ አይተውልሻል ።

15 ፤ ሳምኬት ። መንገድ ፡ ዐላፊዎች ፡ ኹሉ ፡ እጃቸውን ፡ ያጨበጭቡብሻልና ፦ በእውኑ ፡ የውበት ፡ ፍጻሜና ፡ የምድር ፡ ኹሉ ፡ ደስታ ፡ የሚሏት ፡ ከተማ ፡ ይህች ፡ ናትን ፧ እያሉ ፥ በኢየሩሳሌም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ያፏጫሉ ፥ ራሳቸውንም ፡ ያነቃንቃሉ ።

16 ፤ ዔ ። ጠላቶችሽ ፡ ኹሉ ፡ አፋቸውን ፡ አላቀቁብሽ ፤ እያፏጩና ፡ ጥርሳቸውን ፡ እያፋጩ ፦ ውጠናታል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ተስፋ ፡ ያደረግናት ፡ ቀን ፡ ይህች ፡ ናት ፤ አግኝተናታል ፥ አይተናትማል ፡ ይላሉ ።

17 ፤ ፌ ። እግዚአብሔር ፡ ያሰበውን ፡ አደረገ ፤ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ያዘዘውን ፡ ቃል ፡ ፈጸመ ፤ አፈረሰ ፡ አልራራምም ፤ ጠላትንም ፡ ደስ ፡ አሠኘብሽ ፥ የሚያስጨንቁሽንም ፡ ቀንድ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገ ።

18 ፤ ጻዴ ። ልባቸው ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ ጮኸ ፦ የጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ቅጥር ፡ ሆይ ፥ እንባሽን ፡ እንደ ፡ ፈሳሽ ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ አፍሺ ፤ ለሰውነትሽ ፡ ዕረፍት ፡ አትስጪ ፤ የዐይንሽ ፡ ብሌን ፡ አታቋርጥ ።

19 ፤ ቆፍ ። ተነሺ ፥ በሌሊት ፡ በመዠመሪያ ፡ ክፍል ፡ ጩኺ ፥ በጌታም ፡ ፊት ፡ ልብሽን ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ አፍሺ ፤ በጐዳና ፡ ኹሉ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ በራብ ፡ ስለደከሙ ፡ ስለሕፃናትሽ ፡ ነፍስ ፡ እጆችሽን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አንሺ ።

20 ፤ ሬስ ። አቤቱ ፥ እይ ፤ በማን ፡ ላይ ፡ እንደዚህ ፡ እንዳደረግኽ ፡ ተመልከት ። በእውኑ ፡ ሴቶች ፡ ፍሬያቸውን ፥ ያቀማጠሏቸውን ፡ ሕፃናት ፥ ይበላሉን ፧ በእውኑ ፡ ካህኑና ፡ ነቢዩ ፡ በጌታ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ይገደላሉን ፧

21 ፤ ሳን ። ብላቴናውና ፡ ሽማግሌው ፡ በመንገዶች ፡ ላይ ፡ ተጋደሙ ፤ ደናግሎቼና ፡ ጐበዛዝቴ ፡ በሰይፍ ፡ ወድቀዋል ፤ በቍጣኽ ፡ ቀን ፡ ገደልኻቸው ፤ ሳትራራ ፡ ዐረድኻቸው ።

22 ፤ ታው ። እንደ ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ የሚያስፈሩኝን ፡ ከዙሪያዬ ፡ ጠራኽ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ቀንም ፡ ያመለጠ ፡ ወይም ፡ የቀረ ፡ አልተገኘም ፤ ያቀማጠልኹቸውንና ፡ ያሳደግኹቸውን ፡ ጠላቴ ፡ በላቸው ።

## ____________________ሰቆቃወ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 3 ።

1 ፤ አሌፍ ። በቍጣው ፡ በትር ፡ መከራ ፡ ያየ ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

2 ፤ ብርሃን ፡ ወደሌለበት ፡ ወደ ፡ ጨለማ ፡ መርቶ ፡ ወሰደኝ ።

3 ፤ ዘወትር ፡ ቀኑን ፡ ኹሉ ፡ እጁን ፡ በላዬ ፡ መለሰ ።

4 ፤ ቤት ። ሥጋዬንና ፡ ቍርበቴን ፡ አስረጀ ፥ ዐጥንቴን ፡ ሰበረ ።

5 ፤ ቅጥር ፡ ሠራብኝ ፡ በሐሞትና ፡ በድካምም ፡ ከበበኝ ።

6 ፤ ቀድሞ ፡ ሞተው ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ በጨለማ ፡ አኖረኝ ።

7 ፤ ጋሜል ። እንዳልወጣ ፡ በዙሪያዬ ፡ ቅጥር ፡ ሠራብኝ ፤ ሰንሰለቴን ፡ አከበደ ።

8 ፤ በጠራኹና ፡ በጮኽኹ ፡ ጊዜ ፡ ጸሎቴን ፡ ከለከለ ።

9 ፤ መንገዴን ፡ በተጠረበ ፡ ድንጋይ ፡ ዘጋ ፥ ጐዳናዬንም ፡ አጣመመ ።

10 ፤ ዳሌጥ ። እንደሚሸምቅ ፡ ድብ ፡ እንደ ፡ ተሸሽገም ፡ አንበሳ ፡ ኾነብኝ ።



www.ethiopianorthodox.org

11 ፤ መንገዴን ፡ ለወጠ ፥ ገነጣጠለኝም ፤ ባድማ ፡ አደረገኝ ።

12 ፤ ቀስቱን ፡ ገተረ ፡ ለፍላጻውም ፡ እንደ ፡ ጊጤ ፡ አደረገኝ ።

13 ፤ ሄ ። የሰገባውን ፡ ፍላጻዎች ፡ በኵላሊቴ ፡ ውስጥ ፡ ተከለ ።

14 ፤ ለወገኔ ፡ ኹሉ ፡ ማላገጫ ፡ ቀኑንም ፡ ኹሉ ፡ መሳለቂያ ፡ ኾንኹ ።

15 ፤ ምሬት ፡ ሞላብኝ ፡ በሬትም ፡ አጠገበኝ ።

16 ፤ ዋው ። ጥርሴን ፡ በጭንጫ ፡ ሰበረ ፥ በዐመድም ፡ ከደነኝ ።

17 ፤ ነፍሴን ፡ ከሰላም ፡ አራቅኽ ፤ በጎ ፡ ነገርን ፡ ረሳኹ ።

18 ፤ እኔም ፦ ኀይሌ ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ተስፋዬ ፡ ጠፋ ፡ አልኹ ።

19 ፤ ዛይ ። መከራዬንና ፡ ችግሬን ፡ ሬትንና ፡ ሐሞትን ፡ ዐስብ ።

20 ፤ ነፍሴ ፡ እያሰበችው ፡ በውስጤ ፡ ፈዘዘች ።

21 ፤ ይህችን ፡ በልቤ ፡ አኖራለኹ ፥ ስለዚህ ፡ እታገሣለኹ ።

22 ፤ ሔት ። ያልጠፋነው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ምሕረት ፡ የተነሣ ፡ ነው ፤ ርኅራኄው ፡ አያልቅምና ።

23 ፤ ማለዳ ፡ ማለዳ ፡ ዐዲስ ፡ ነው ፤ ታማኝነትኽ ፡ ብዙ ፡ ነው ።

24 ፤ ነፍሴ ፦ እግዚአብሔር ፡ ዕድል ፡ ፈንታዬ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፥ ተስፋ ፡ አደርገዋለኹ ፡ አለች ።

25 ፤ ጤት ። እግዚአብሔር ፡ በተስፋ ፡ ለሚጠብቁት ፡ ለምትሻውም ፡ ነፍስ ፡ መልካም ፡ ነው ።

26 ፤ ሰው ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ማዳን ፡ ተስፋ ፡ ቢያደርግ ፡ መልካም ፡ ነው ።

27 ፤ ሰው ፡ በታናሽነቱ ፡ ቀንበር ፡ ቢሸከም ፡ መልካም ፡ ነው ።

28 ፤ ዮድ ። ርሱ ፡ አሸክሞታልና ፥ ዝም ፡ ብሎ ፡ ለብቻው ፡ ይቀመጥ ።

29 ፤ ተስፋ ፡ የኾነው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አፉን ፡ በዐፈር ፡ ውስጥ ፡ ያኑር ።

30 ፤ ጕንጩን ፡ ለሚመታው ፡ ይስጥ ፥ ስድብንም ፡ ይጥገብ ።

31 ፤ ካፍ ። ጌታ ፡ ለዘለዓለም ፡ አይጥልምና ፤

32 ፤ ቢያሳዝንም ፡ እንደ ፡ ምሕረቱ ፡ ብዛት ፡ ይራራልና ፤

33 ፤ የሰውን ፡ ልጆች ፡ ከልቡ ፡ አያስጨንቅም ፥ አያሳዝንምም ።

34 ፤ ላሜድ ። በምድር ፡ የተጋዙትን ፡ ኹሉ ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ ይረግጣቸው ፡ ዘንድ ፥

35 ፤ የሰውን ፡ ፍርድ ፡ በልዑል ፡ ፊት ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፥

36 ፤ የሰውን ፡ ፍርድ ፡ ያጣምም ፡ ዘንድ ፡ ጌታ ፡ ዕሺ ፡ አይልም ።

37 ፤ ሜም ። ጌታ ፡ ያላዘዘውን ፡ የሚልና ፡ የሚፈጽም ፡ ማን ፡ ነው ፥

38 ፤ ከልዑል ፡ አፍ ፡ ክፉና ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ አይወጣምን ፥

39 ፤ ሕያው ፡ ሰው ፡ የሚያጕረመርም ፥ ሰው ፡ ስለኀጢአቱ ፡ ቅጣት ፡ የሚያጕረመርም ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፥

40 ፤ ኖን ። መንገዳችንን ፡ እንመርምርና ፡ እንፈትን ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንመለስ ።

41 ፤ ልባችንን ፡ ከእጃችን ፡ ጋራ ፡ በሰማይ ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እናንሣ ።

42 ፤ በድለናል ፡ ዐምፀናልም ፥ አንተም ፡ ይቅር ፡ አላልኽም ።

43 ፤ ሳምኬት ። በቍጣ ፡ ከደንኽን ፡ አሳደድኽንም ፤ ገደልኽን ፥ አልራራኽም ።



www.ethiopianorthodox.org

44 ፤ ጸሎት ፡ እንዳያልፍ ፡ ራስኽን ፡ በደመና ፡ ከደንኽ ።

45 ፤ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ጕድፍና ፡ ውዳቂ ፡ አደረግኸን ።

46 ፤ ፄ ። ጠላቶቻችን ፡ ዅሉ ፡ አፋቸውን ፡ አላቀቁብን ።

47 ፤ ድንጋጤና ፡ ቍጣ ፥ ጥፋትና ፡ ቅጥቃጤ ፡ ኾነብን ።

48 ፤ ስለወገኔ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ቅጥቃጤ ፡ ዐይኔ ፡ የውሃ ፡ ፈሳሽ ፡ አፈሰሰች ።

49 ፤ 50 ፤ ፌ ። እግዚአብሔር ፡ ከሰማይ ፡ እስኪጐበኝና ፡ እስኪመለከት ፡ ድረስ ፡ ዐይኔ ፡ ሳታቋርጥ ፡ ዝም ፡ ሳትል ፡ እንባ ፡ ታፈስሳለች ።

51 ፤ ስለከተማዬ ፡ቈነጃጅት ፡ ዅሉ ፡ ዐይኔ ፡ ነፍሴን ፡ አሳዘነች ።

52 ፤ ጻዴ ። በከንቱ ፡ ነገር ፡ ጠላቶች ፡ የኾኑኝ ፡ እንደ ፡ ወፍ ፡ ማደንን ፡ አደኑኝ ።

53 ፤ ሕይወቴን ፡ በጕድጓድ ፡ አጠፉ ፥ በላዬም ፡ ድንጋይ ፡ ጣሉ ።

54 ፤ በራሴ ፡ ላይ ፡ ውሃዎች ፡ ተከነበሉ ፤ እኔም ፦ ጠፋኹ ፡ ብዬ ፡ ነበር ።

55 ፤ ቆፍ ። አቤቱ ፥ በጠለቀ ፡ ጕድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ኾኜ ፡ ስምኽን ፡ ጠራኹ ።

56 ፤ ድምፄን ፡ ሰማኽ ፤ ጕሮኽን ፡ ከልመናዬ ፡ አትመልስ ።

57 ፤ በጠራኹኽ ፡ ቀን ፡ ቀርበኽ ፦ አትፍራ ፡ አልኽ ።

58 ፤ ሬስ ። ጌታ ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ ነፍሴ ፡ ተሟግተኽ ፡ ሕይወቴን ፡ ተቤዥኽ ።

59 ፤ አቤቱ ፥ ጭንቀቴን ፡ አይተኻል ፥ ፍርዴን ፡ ፍረድልኝ ።

60 ፤ በቀላቸውን ፡ ዅሉና ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ዐሳባቸውን ፡ ዅሉ ፡ አየኽ ።

61 ፤ ሳን ። አቤቱ ፥ ስድባቸውንና ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ዐሳባቸውን ፡ ዅሉ ፥

62 ፤ የተነሡብኝን ፡ ሰዎች ፡ ከንፈሮች ፡ ቀኑንም ፡ ዅሉ ፡ ያሰቡብኝን ፡ ዐሳባቸውን ፡ ሰማኽ ።

63 ፤ መቀመጣቸውንና ፡ መነሣታቸውን ፡ ተመልከት ፤ እኔ ፡ መሳለቂያቸው ፡ ነኝ ።

64 ፤ ታው ። አቤቱ ፥ እንደ ፡ እጃቸው ፡ ሥራ ፡ ፍዳቸውን ፡ ትከፍላቸዋለኽ ።

65 ፤ የልብ ፡ ዕውርነትንና ፡ ርግማንኽን ፡ ትሰጣቸዋለኽ ።

66 ፤ አቤቱ ፥ በቍጣ ፡ ታሳድዳቸዋለኽ ፡ ከሰማይም ፡ በታች ፡ ታጠፋቸዋለኽ ።

ሰቆቃወ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ምዕራፍ ፡ 4 ።

1 ፤ አሌፍ ። ወርቁ ፡ እንዴት ፡ ደበሰ! ጥሩው ፡ ወርቅ ፡ እንዴት ፡ ተለወጠ! የመቅደሱ ፡ ድንጋዮች ፡ በጐዳና ፡ ዅሉ ፡ ራስ ፡ ተበተኑ ።

2 ፤ ቤት ። ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ የሚመስሉ ፡ የከበሩ ፡ የጽዮን ፡ ልጆች ፥ የሸክላ ፡ ሠሪ ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ሠራው ፡ እንደ ፡ ሸክላ ፡ ዕቃ ፡ እንዴት ፡ ተቈጠሩ!

3 ፤ ጋሜል ። ቀበሮዎች ፡ እንኳ ፡ ጡቶታቸውን ፡ ገልጠው ፡ ግልገሎቻቸውን ፡ አጠቡ ፤ የወገኔ ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ሰጐን ፡ ጨካኝ ፡ ኾነች ።

4 ፤ ዳሌጥ ። ጡት ፡ የሚጠባው ፡ የሕፃን ፡ ምላስ ፡ ከጥም ፡ የተነሣ ፡ ወደ ፡ ትናጋው ፡ ተጣበቀ ፤ ሕፃናት ፡ እንጀራ ፡ ለመኑ ፥ የሚቈርስላቸውም ፡ የለም ።

5 ፤ ሄ ። የጣፈጠ ፡ ነገር ፡ ይበሉ ፡ የነበሩ ፡ በመንገድ ፡ ጠፉ ፤ በቀይ ፡ ግምጃ ፡ ያድጉ ፡ የነበሩ ፡ የፍግ ፡ ክምር ፡ ዐቀፉ ።



www.ethiopianorthodox.org

6 ፤ ዋው ። የማንም ፡ እጅ ፡ ሳይወድቅባት ፡ ድንገት ፡ ከተገለበጠች ፡ ከሰዶም ፡ ኀጢአት ፡ ይልቅ ፡ የወገኔ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ኀጢአት ፡ በዛች ።

7 ፤ ዛይ ። አለቃዎቿ ፡ ከበረዶ ፡ ይልቅ ፡ ጥሩ ፥ ከወተት ፡ ይልቅ ፡ ነጭ ፡ ነበሩ ፤ ገላቸው ፡ ከቀይ ፡ ዕንቍ ፡ ይልቅ ፡ ቀይ ፡ ነበረ ፥ መልካቸውም ፡ እንደ ፡ ሰንፔር ፡ ነበረ ።

8 ፤ ሔት ። ፊታቸው ፡ ከጥቀርሻ ፡ ይልቅ ፡ ጠቍሯል ፥ በመንገድም ፡ አልታወቁም ፤ ቍርበታቸው ፡ ወደ ፡ ዐጥንታቸው ፡ ተጣብቋል ፤ ደርቋል ፤ እንደ ፡ ዕንጨት ፡ ኾኗል ።

9 ፤ ጤት ። በሰይፍ ፡ የሞቱ ፡ በራብ ፡ ከሞቱት ፡ ይሻላሉ ፤ እነዚህ ፡ የምድርን ፡ ፍሬ ፡ ዐጥተው ፡ ተወግተውም ፡ ቀጥነዋል ።

10 ፤ ዮድ ። የርኅሩኆች ፡ ሴቶች ፡ እጆች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ቀቅለዋል ፤ የወገኔ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ በመቀጥቀጧ ፡ መብል ፡ ኾኗቸው ።

11 ፤ ካፍ ። እግዚአብሔር ፡ መዓቱን ፡ ፈጽሟል ፥ ጽኑ ፡ ቍጣውን ፡ አፍስሷል ፤ እሳትን ፡ በጽዮን ፡ ውስጥ ፡ አቃጠለ ፥ መሠረቷንም ፡ በላች ።

12 ፤ ላሜድ ። የምድር ፡ ነገሥታት ፡ በዓለምም ፡ የሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ አስጨናቂና ፡ ጠላት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በር ፡ እንዲገባ ፡ አላመኑም ።

13 ፤ ሜም ። የጻድቃንን ፡ ደም ፡ በውስጧ ፡ ስላፈሰሱ ፡ ስለነቢያቷ ፡ ኀጢአትና ፡ ስለካህናት ፡ በደል ፡ ነው ።

14 ፤ ኖን ። ታውረው ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ተቅበዘበዙ ፤ ልብሳቸው ፡ እንዳይዳሰስ ፡ በደም ፡ ረክሰዋል ።

15 ፤ ሳምኬት ። እናንተ ፡ ርኩሳን ፥ ራቁ ፥ ርቃችኹም ፡ ኺዱ ፥ አትንኩ ፡ ብለው ፡ ጮኹባቸው ። በሸሹና ፡ በተቅበዘበዙ ፡ ጊዜ ፥ በአሕዛብ ፡ መካከል ። በዚህ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይኖሩም ፡ ተባለ ።

16 ፤ ዔ ። የእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በተናቸው ፡ ርሱም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይመለከታቸውም ፤ የካህናቱን ፡ ፊት ፡ አላፈሩም ፥ ሽማግሌዎቹንም ፡ አላከበሩም ።

17 ፤ ፌ ። ዐይናችን ፡ ወደ ፡ ከንቱ ፡ ረዳታችን ፡ ገና ፡ ሲመለከት ፡ ጠፍቷል ፤ በመቈየታችን ፡ ማዳን ፡ የማይቻለውን ፡ ሕዝብ ፡ ጠብቀናል ።

18 ፤ ጻዴ ። በአደባባያችን ፡ እንዳንኼድ ፡ ፍለጋችንን ፡ ተከተሉ ፤ ፍጻሜያችን ፡ ቀርቧል ፥ ዕድሜያችን ፡ አልቋል ፥ ፍጻሜያችን ፡ ደርሷል ።

19 ፤ ቆፍ ። አሳዳጆቻችን ፡ ከሰማይ ፡ ንስር ፡ ይልቅ ፡ ፈጣኖች ፡ ኾኑ ፤ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ አሳደዱን ፥ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሸመቁብን ።

20 ፤ ሬስ ። ስለ ፡ ርሱ ፦ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ በጥላው ፡ በሕይወት ፡ እንኖራለን ፡ ያልነው ፡ በእግዚአብሔር ፡ የተቀባ ፥ የሕይወታችን ፡ እስትንፋስ ፥ በጕድጓዳቸው ፡ ተያዘ ።

21 ፤ ሳን ። በዖፅ ፡ ምድር ፡ የምትኖሪ ፡ የኤዶምያስ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ደስ ፡ ይበልሽ ፡ ሐሤትም ፡ አድርጊ ፤ ጽዋው ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ያልፋል ፥ አንቺም ፡ ትሰክሪያለሽ ፡ ትራቈቻለሽም ።

22 ፤ ታው ። የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የበደልሽ ፡ ቅጣት ፡ ተፈጸመ ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አያስማርክሽም ። የኤዶምያስ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ በደልሽን ፡ ይቀጣል ፤ ኀጢአትሽን ፡ ይገልጣል ።

## ሰቆቃወ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ምዕራፍ ፡ 5 ።

1 ፤ አቤቱ ፥ የኾነብንን ፡ ዐስብ ፤ ተመልከት ፡ ስድባችንንም ፡ እይ ።

2 ፤ ርስታችን ፡ ለእንግዳዎች ፥ ቤቶቻችን ፡ ለሌላዎች ፡ ኾኑ ።

3 ፤ ድኻ ፡ አደጎችና ፡ አባት ፡ የሌለን ፡ ኾነናል ፤ እናቶቻችን ፡ እንደ ፡ መበለቶች ፡ ኾነዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

4 ፤ ውሃችንን ፡ በብር ፡ ጠጣን ፡ ዕንጨታችንን ፡ በዋጋ ፡ ገዛን ።

5 ፤ አሳዳጆቻችን ፡ በዐንገታችን ፡ ላይ ፡ ናቸው ፤ እኛ ፡ ደክመናል ፡ ዕረፍትም ፡ የለንም ።

6 ፤ ለግብጻውያንና ፡ ለአሶራውያን ፡ እንጀራ ፡ እንጠግብ ፡ ዘንድ ፡ እጅ ፡ ሰጠን ።

7 ፤ አባቶቻችን ፡ ኀጢአትን ፡ ሠሩ ፡ ዛሬም ፡ የሉም ፤ እኛም ፡ በደላቸውን ፡ ተሸከምን ።

8 ፤ ባሪያዎች ፡ ሠልጥነውብናል ፤ ከእጃቸው ፡ የሚታደገን ፡ የለም ።

9 ፤ ከምድረ ፡ በዳ ፡ ሰይፍ ፡ የተነሣ ፡ በሕይወታችን ፡ እንጀራችንን ፡ እናመጣለን ።

10 ፤ ከሚያቃጥል ፡ ከራብ ፡ ትኵሳት ፡ የተነሣ ፡ ቍርበታችን ፡ እንደ ፡ ምድጃ ፡ ጠቈረ ።

11 ፤ በጽዮን ፡ ሴቶችን ፣ በይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ ደናግልን ፡ አጐሰቈሉ ።

12 ፤ አለቃዎች ፡ በእጃቸው ፡ ተሰቀሉ ፤ የሽማግሌዎች ፡ ፊት ፡ አልታፈረም ።

13 ፤ ጕልማሳዎች ፡ ወፍጮን ፡ ተሸከሙ ፣ ልጆችም ፡ ከዕንጨት ፡ በታች ፡ ተሰናከሉ ።

14 ፤ ሽማግሌዎች ፡ ከአደባባይ ፣ ጕልማሳዎች ፡ ከበገናቸው ፡ ተሻሩ ።

15 ፤ የልባችን ፡ ደስታ ፡ ቀርቷል ፤ ዘፈናችን ፡ ወደ ፡ ልቅሶ ፡ ተለውጧል ።

16 ፤ አክሊል ፡ ከራሳችን ፡ ወድቋል ፤ ኀጢአት ፡ ሠርተናልና ፣ ወዮልን!

17 ፤ ስለዚህ ፣ ልባችን ፡ ታሟል ፤ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ ዐይናችን ፡ ፈዟል ፤

18 ፤ ስለጽዮን ፡ ተራራ ፣ ባድማ ፡ ኾናለችና ፣ ቀበሮዎችም ፡ ተመላልሰውባታልና ።

19 ፤ አቤቱ ፣ አንተ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኖራለኽ ፤ ዙፋንኽ ፡ ከትውልድ ፡ እስከ ፡ ትውልድ ፡ ነው ።

20 ፤ ስለ ፡ ምን ፡ ለዘለዓለም ፡ ትረሳናለኽ ፧ ስለ ፡ ምንስ ፡ ለረዥም ፡ ዘመን ፡ ትተወናለኽ ፧

21 ፤ አቤቱ ፣ ወዳንተ ፡ መልሰን ፡ እኛም ፡ እንመለሳለን ፤ ዘመናችንን ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ ዐድስ ።

22 ፤ ነገር ፡ ግን ፣ ፈጽመኽ ፡ ጥለኸናል ፤ እጅግ ፡ ተቈጥተኸናል ፨

http://www.gzamargna.net

www.ethiopianorthodox.org